# የጊታር ትምህርት መማሪያ

*GOSPEL MEDIA & MUSIC MINISTRY*(GMM)

ወንጌል በሚዲያና የሙዚቃ አገልግሎት (ጂ.ኤም.ኤም)

አዘጋጆች ዮናስ ጎርፌ
ዮናስ ጌታቸው

1990 ( 1998 ) ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

ብዙ ሰዎች ሙዚቃን መማር እንደ ቀላል ነገር አድርገው ይወስዱታል።ነገር ግን ጥልቀት ያለውና የረቀቀ የሙዚቃ ተጫዋች ለመሆን እጅግ አድካሚና ጊዜም የሚፈልግ ነው።ብዙዎች የሀገራችን ወጣት ሙዚቀኞች ይህንን ሳይረዱ ኪቦርድ በሚፈጥረው የማሽን ድምፅ ጋጋታ በመርካት ችሎታቸውን ሙዚቃዊ ሕግ በሚፈቅደው መንገድ ባለማሳደጋቸው እውቀታቸው በጣም ቁንጽል ሆኖ ይታያል። በተለይም በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ ያሉ ወጣት ሙዚቀኞች ያላቸው የሙዚቃ እውቀት በአያሌው ሊጎለብት የሚገባው ብዙ ነገር አለው። ስለሆነም የዚህ መጽሐፍ ዋና ዓላማ ወጣቶቻችን ጊታርን በአግባቡና ሙዚቃዊ ሕግጋትን በተከተለ መንገድ እንዲማሩ ለማድረግና በተጨማሪም መጠነኛ የሆነ የሙዚቃ ቲዎሪ እንዲቀስሙ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። በመፅሐፉም መጨረሻ ላይ በርከት ያሉ የተለያዩ የፒያኖ ኮርዶችን በመጨመር ሙዚቀኞቹ ከተለመዱት ኮርዶች ወጣ በማለት እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ እንደሚረዳቸው ተስፋ እናደርጋለን።

ይህንን መፅሐፍ በምናዘጋጅበት ጊዜ የተለያዩ ሐሳቦችን በመስጠት እንዲሁም እርማትን በማድረግ ለተባበራችሁን ሁሉ ከልብ የጠለቀ ምስጋና እናቀርባለን። በተለይም ደግሞ ለዕዝራ አባተ ለዮሐንስ ጦና (ጆኒ) ለኤልያስ መልካ ለአበበ ከበደ እና ለደረሰ ብሩ ልዩ ምስጋናችንን ልናቀርብ እንወዳለን።ሆኖም በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ለሚኖረው ማንኛውም ስሕተት ሁሉ ኃላፊነቱ የአዘጋጆቹ ነው።

ዮናስ ጎርፌ (ጂ.ኤም.ኤም ዲሬክተር)

## የጊታር ትምህርት መምሪያ

ጊታር መማር ቀላል ነው? ለመማር ብዙ ጊዜ ይፈጅ ይሆን? ዛሬ የጊታር ትምህርት መማር ብጀምር ከአንድ ሳምንት በኋላ ከመዘምራን ጋር ልጫወት እችላለሁ?።

ከላይ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች አዎንታዊ ወይንም አሉታዊ መልስ መስጠት ይቻላል። መልሶቹ ግን እንደ ፍላጎትህና/ሽና/ እንደ ጥረትህ/ሽ/ ሊወሰን ይችላል። ምክንያቱም አንድ የሙዚቃ መሳሪያን ለመማር ወሳኝ የሚሆነው የምታደርገው/ጊው/ የዕለት ተዕለት ልምምድና ጥረት ነው። በተጨማሪም ሊዘነጋ የማይገባው ነገር ቢኖር፣ ያለህም/ሽም/ የተፈጥሮ የሙዚቃ ዝንባሌ ትልቅ ስፍራ እንዳለው ነው። አንድ ሰው ጊታር ሲጫወት ስታይ/ዪ/ ወይም ስትሰማ/ሚ/ በጣም ቀላል ይመስልህ/ሽ/ ይሆናል። ሆኖም ስትሞክረው/ሪው/ ቀላል ሆኖ አታገኘውም/ኚውም/። ቢሆንም ተስፋ ሳትቆርጥ/ጪ/ ልምምድህን/ሽን/ ዕለት በዕለት ልትቀጥል/ዪ/ ይገባል። ምክንያቱም ዛሬ ጥሩ ተጫዋች ሆኖ የምታየው/ዪው/ ሙዚቀኛ ሁሉ አንድ ቀን እዳንተው/ቺው/ ጀማሪ እንደ ነበረ አትዘንጋ/ጊ/። ስለዚህ ሳታቋርጥ/ርጪ/ ተለማመድ/ጂ/።

ሌላው ስለ ሙዚቃ ስናወሳ በጣም አስፈላጊ የሆነው ነገር ማዳመጥ ነው። ይህም ማለት ምን ጊዜም ስትጫወት/ቺ/ የምትጫወተውን/ቺውን/ ሙዚቃ በጥንቃቄና በማስተዋል የማዳመጥ ችሎታህን/ሽን/ ማዳበር ይገባሃል/ሻል/። ይህ መልካም ልምድ ከሌለህ/ሽ/ ጥሩ የጊታር ተጫዋች መሆን አትችልም/ቺዪም/። ይህ መጽሐፍ ጊታር ለመጫወት ይረዳህ/ሽ/ ዘንድ መሠረታዊ ሐሳቦችን ትሰጥሃለች/ሻለች/። ገጽ በገጽ መመሪያውን እየተከተልክ/ሽ/ ተለማመድ/ጂ/። ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር ቢያጋጥምህ/ሽ/ እንኳን ልምምድህን/ሽን/ በፍጹም አታስተጓጉል/ዪ/። ማስታወስ የሚገባህ/ሽ/ ነገር ቢኖር፣ አንድ የሙዚቃ መሳሪያ ለመማር ጊዜና ከባድ ጥረትን ይጠይቃል።

## ለጊታር ጥንቃቄ ማድረግ

በመሠረቱ ሁለት ዓይነት ጊታሮች አሉ። ፕለክትረም (plectrum) የተባለ ባለ ሽቦ አውታር (string) ጊታርና ስፓኒሽ (Spanish) ጊታር የተባለ ባለናይለን አውታር ጊታር ነው። ከእነዚህ ከሁለት ዓይነት ጊታሮች በፈለከው/ግሽው/ ጊታር መማር ትችላለህ/ያለሽ/። ማስታወስ የሚኖርብህ/ሽ/ ግን ለናይለን ጊታር በተሠሩ ጊታሮች ላይ ባለ ሽቦ አውታር ማስገባት የለብህም/ሽም/። ብዙውን ጊዜ ባለ ናይለን ጊታሮች ከባለ ሽቦዎቹ ይልቅ ቀለል ብለው የሚሠሩ ናቸው። ስለዚህም በእነዚህ ቀለል ባሉ ጊታሮች ላይ ባለ ሽቦ አውታር ማስገባት የሽቦው ውጥረት ኃይለኛ ስለሚሆን እንደገና ሊታደስ በማይቻል ሁኔታ ሊያበላሸው ይችላል። በባለ ሽቦ ጊታር ላይ ናይለን አውታር ቢወጠር ምንም ጉዳት አያስከትልበትም። ሆኖም ብዙውን ጊዜ ጥሩ ድምጽ አይሰጥም። ሁል ጊዜ ጊታርህን/ሽን/ በጥንቃቄ መያዝ ከተለያዩ ጉዳቶች ይጠብቀዋል። ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ ጊታርህ/ሽ/ ቢጎዳ ሊጠገን የማይችል ጉዳት ሊደርስበት ይችላል። ብልሽት ከደረሰበት በኃላ ቢጠገን እንኳን የተጠገነው ጊታር እንደ በፊቱ ጥሩ ድምጽ ሊሰጥ አይችልም ይሆናል። ጊታርህን/ሽን/ በፀሐይ ውስጥና እርጥበት ባለው ቦታ አታስቀምጥ/ጪ/። ሀይለኛ ሙቀት ወይንም እርጥበት የጊታሩን ሳጥን ወይንም እንጨት ሊጎዳው ይችላል።


## የጊታር ኮርዶችን ማንበብ

ጊታርን በተለያዩ መንገዶች ልትጫወት/ቺ/ ትችላለህ/ያለሽ/።በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው የጊታር አጨዋወት ስልት እንዴት መዝሙሮችን በኮርድ ማጀብ እንደምትችል/ቺዪ/ ያሳያል።

እነዚህን ኮርዶች ከስእሎቹ ላይ በማየት ኮርዶቹን መማር ይቻላል። የስእሉ አገላለጽ ወይንም አነባበብ፤ ከላይ ወደታች ወይንም ከታች ወደ ላይ የተሰመሩት መስመሮች የጊታሩን ክሮች ይወክላሉ። ለምሳሌ ያህል 6ኛ 5ኛ 4ኛ. . .ወዘተ እያልክ/ሽ/ ከላይ ወደ ታች ማንበብ ትችላለህ/ያለሽ/። ስድስተኛው ወፍራሙ ክር ሲሆን አንደኛው ደግሞ ቀጭኑ ክር ነው። አግድም የተሰመሩት መስመሮች ደግሞ ፍሬትስ (frets) ይባላሉ።




ከጊታሩ ላይ ያሉት ሁለት ድርብ መስመሮች ደግሞ ነት (nut) ይባላሉ። ቁጥር የተጻፈባቸው ክበቦች ደግም ጣቶችህን ዬት እንደምታሳርፍ/ፊ/ ያመለክታሉ። ቁጥሮቹ ደግሞ የግራ ጣቶችህን/ሽን/ ያመለከታሉ። (ስእሎቹን ተመልከት/ቺ/)።ጣቶችህ/ቺሽ/ የጊታሩን ክር በሚይዙበት ጊዜ ከፍሬቱ በስተጀርባ እንጂ ከፍሬቱ ፊት ለፊት ወይንም በፍሬቱ ላይ መሆን የለባቸም።




## ቅኝት

ጊታርህ/ሽ/ በትክክል ካልተቃኘ የምትጫወተው/ቺው/ ኮርድ ትክክለኛ ድምጽ አይሰጥም። ስለሆነም የመጀመሪያው ተግባርህ/ሽ/ ጊታርህን/ሽን/ መቃኘት ነው። ጊታርህን በፒያኖ፥ በሲንተሳይዘር፥ በአኮርዲዮን ወይንም ለመቃኛ ተብለው በተሰሩ መሳሪያዎች (twiners)

መቃኘት ትችላለህ/ያለሽ/። ከዚህ በታች በስዕል የተመለከተው መግለጫ ጊታርህን/ሽን/ ከኪቦርድ መሳሪያ ጋር አመሳስለህ/ሽ/ ለመቃኘት እንድትችል/ችዪ/ አስፈላጊውን ድምጾች ያመለክታል።





## የርስ በርስ ቅኝት

ከላይ በተጠቀሱት የሙዚቃ መሳሪያዎች ጊታርህን/ሽን/ ከቃኘህ/ሽ/ በኋላ ጊታርህን/ሽን/ እርስ በእርስ የመቃኘት ዘዴ በጣም ጠቃሚና አጥጋቢ ውጤትን የሚሰጥ፥ ጊታርህም/ሽም/ በደንብ መቃኘቱን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም ቅኝቶችን ልብ ብለህ/ሽ/ የማዳመጥ ችሎታህን/ሽን/ እንድታዳብር/ሪ/ ይረዳሃል/ሻል/።



ሆኖም ጊታርህን እርስ በእርስ መቃኘት ከመጀመርህ/ርሽ/ በፊት ልብ ልትለው/ዪው/ የሚገባ ነገር ቢኖር፥የመጀመሪያው ክር ኢ( E ) በደንብ መቃኘቱን እርግጠኛ ሁን/ኚ/። የአቀኛኘቱም ዘዴ የመጀመሪያውን ክር ማለትም ኢን( E ) ክፍት ትተህ/ሽ/ ከሁለተኛው ክር ቢ ( B ) አምስተኛው ፍሬት ላይ በመያዝ ድምፁን አመሳስለህ/ሽ/ ቃኘው/ኚው/። በዚህ መሠረት ስዕሉን መመሪያ በማድረግ ሌሎቹንም ክሮች እርስ በእርስ ለመቃኘት ትችላለህ/ያለሽ/። እንዲሁም በመጀሪያው ክር አማካይነት ሁሉንም ክሮች መቃኘት ትችላለህ/ያለሽ/።




## የቀኝ እጅ ቴክኒክ

ቀኝ እጅህ/ሽ/ የመዝሙሩን ምት (rhythm) ይጫወታል። ጊታርህን/ሽን/ ስትጫወት/ቺ/ በጣቶችህ/ቿሽ/ ወይንም በፒክ (pick) ልትጠቀም/ሚ/ ትችላለህ/ያለሽ/።ሆኖም ዋናው ቁም ነገር ከጊታርህ/ሽ/ ጥሩ ቃና ወይንም ድምፅ ማግኘትህ/ሽ/ ወይንም መስማትህ/ሽ/ ነው። ጂ(G) ኮርድን ያዝና/ዢና/፡-(የዚህን ኮርድ አያያዝ በገፅ ፲ ላይ ይገኛል።)

1. እያንዳንዱን ክሮች ተራ በተራ በአውራ ጣትህ/ሽ/ ከላይ ወደታች እንዲሁም በአመልካች ጣትህ/ሽ/ ከታች ወደ ላይ ምታ/ቺ/። በፒክ የምትጠቀም/ሚ/ ከሆነ ከላይ ወደ ታች ከታች ወደ ላይ በመጫወት ሁሉም ክሮች የጠራ ድምፅ መስጠታቸውን አረጋግጥ/ጪ/።

2. ጊታሩን በምትጫወትበት/ቺበት/ ጊዜ የቀኝ እጅህ/ሽ/ በጊታሩ መስኮት አቅጣጫ መሆን እዳለበት አትዘንጋ/ጊ/።

3. ጊታሩን በምትጫወትበት/ቺበት/ ጊዜ አውራ ጣትህና/ሺና/ አመልካች ጣትህ/ሽ/ ወይንም የምትጫወትበት/ቺበት/ ፒክ ትክክለኛውን መስመር ይዘህ/ሽ/ ልትጫወት/ቺ/ ይገባል። ይህም ማለት በቀጥታ ወደ ታችና ወደ ላይ አግድም ሳትሄድ መጫወት አለብህ/ሽ/ ማለት ነው።

ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በመከተል ደጋግመህ/ሽ/ ለብዙ ጊዜ ተለማመድ/ጂ/። የምትጫወታቸው/ቺቸው/ ክሮች በሙሉ የጠራ ድምፅ መስጠት አለባቸው። አንዱ ክር ከሌላው ክር የበለጠ ድምጽ መስጠት የለበትም። የምትጫወተውን/ቺውን/ ድምፅ ልብ ብለህ/ሽ/ አድምጥ/ጪ/። ምናልባት ጣቶችህ/ሽ/ ክሮቹን በደንብ መያዝ እስኪለምዱ ድረስ የተጣራ ድምጽ ማግኘት ያስቸግርህ/ሽ/ ይሆናል። ሆኖም ተስፋ ሳትቆርጥ/ጪ/ ልምምድህን/ሽን/ ቀጥል/ዪ/። በአውራ ጣትህ/ሽ/ ወደታች በአመልካች ጣትህ/ሽ/ ወደ ላይ በመምታት አንድ ሙሉ ምት (rhythm) ተጫወት/ቺ/።በፒክም የምትጫወት/ቺ/ ከሆነ ወደ ታች አንዴ መትተህ/ሽ/ ወደ ላይ ስትመለስ/ሺ/ አንድ ሙሉ ሪትም ተጫወትክ/ሽ/ ይባላል። ይህንን አይነት ሪትም ጣቶችህ ጥራት ያለው ድምጽ እስኪሰጡህ/ሽ/ ድረስ ደጋግመህ/ሽ/ ተለማመድ/ጂ/።

## <u>ለቀማ (picking)</u>

ጂ(G) ኮርድ ያዝና/ዢና/ (የዚህን ኮርድ አያያዝ በገፅ ፺ ላይ ይገኛል።) አውራ ጣትህን/ሽን/ በስድስተኛው ክር(E) ላይ አስቀምጥ/ጪ/። የአመልካች ጣትህን/ሽን/ በሦስተኛው ክር(G) ላይ አስቀምጥ/ጪ/። የመሐከለኛ ጣትህን/ሽን/ በሁለተኛው ክር(B) ላይ አስቀምጥ/ጪ/።




የቀለበት ጣትህን/ሽን/ ደግሞ በአንደኛው ክር(E) ላይ አስቀምጥ/ጪ/። ከዚያም ጣቶችህ/ሽ/ ብቻ ያረፈባቸውን ክሮች ተራ በተራ እየለቀምክ/ሽ/ ተጫወት/ቺ/። ይህ ዓይነት ጨዋታ የቀኝ ጣቶችህን/ሽን/ የሚያፍታታ ሲሆን በግራ ጣቶችህም/ሽም/ የያዝካቸውን/ዣቸውን/ ክሮች በደንብ መያዝ እንድትችል/ዪ/ ያለማምዱሃል/ሻል/። የለቀማ (picking) ጨዋታ ልምምድህን ደጋግመህና/ሽና/ አዘውትረህ/ሽ/ አድርግ/ጊ/።

## ኮርድ ወይንም ሕብረ ድምፅ

ሶስት ወይንም ከሶስት በላይ የሆኑ ድምፆችን በአንድነት ስትጫወት/ቺ/ የምታገኘው/ኚው/ ሕብረ ድምፅ ኮርድ ተብሎ ይጠራል። (አንድ አንዶች ደግሞ ሁለት ወይም ከሁለት ድምፆች በላይ ኮርድ ይፈጥራል ይላሉ።) ለምሳሌ ያህል፤ G - B - D ድምፆችን በአንድ ላይ ብትጫወት/ቺ/ የGን ኮርድ ይፈጥርልሃል/ሻል/። በማንኛውም መዝሙር ውስጥ መሠረታዊ የሆኑ ሦስት በዋናነት የሚያገለግሉ ሜጀር ወይንም ማይነር ኮርዶች አሉ። ለብዙ መዝሙራት እነዚህን ኮርዶች መጠቀም ይቻላል። ለምሳሌ ያህል መዝሙሩ በG ሜጀር ኮርድ ላይ የተመሰረተ ከሆነ C ሜጀርና D7 ሜጀርን እንዲሁም ሌሎች ማይነር ኮርዶችን በተቀጽላነት ወይም በአጫፋሪነት ልትጠቀምባቸው ትችላለህ/ያለሽ/። እንዲሁም መዝሙሩ በማይነር ኮርዶች ላይ የተመሰረተ ከሆነ ተቀጽላ ወይንም አጫፋሪ ማይነር ኮርዶችን ልትጠቀምባቸው ትችላለህ/ያለሽ/። ለምሳሌ ያህል መዝሙሩ በA ማይነር ኮርድ ላይ የተመሰረተ ከሆነ D ማይነርንና E ማይነርን ወይም E7 ሜጀርን በተቀጽላ ወይም በአጫፋሪነት ልትጠቀምባቸው ትችላለህ/ያለሽ/።ሆኖም የመዝሙሩ ሕብረ ድምጽ (harmony) የበለጠ ውስብስብ ከሆነ እነዚህን ሶስት ቁልፍ ኮርዶች መሰረት በማድረግ ተጨማሪ ሜጀር፣ ማይነር፥ ኦግመንትድ፥ ድምንሽድ ወዘተ..... ኮርዶችን መጠቀም ይቻላል።ከዚህ በታች በሚታዩት ሶስት ኮርዶች ጣቶችህን/ሽን/ ለማፍታታት እንዲረዳህ/ሽ/ ቀስ ብለህ/ሽ/ የተጣራ ድምፅ እስከታገኝ/ኚ/ ድረስ ተራ በተራ ተለማመዳቸው/ጃቸው/።

በደንብ ካጠናኻቸው/ሻቸው/ በኋላ ከG ወደ C ከC ወደD7 ከD7 ወደG ጣቶችህን/ሽን/ እያቀያየርክ/ሽ/ ተለማመድ/ጂ/። በምትለማመድበት/ጂበት/ ጊዜ በመጀመሪያ አራት ጊዜ እየቆጠርክ/ሽ/ ሙሉ ምት ተለማመድ/ጂ/። አራት ጊዜ ምት ሲቀልህ/ሽ/ ሦስት ጊዜ እየመታህ/ሽ/ ከዚያም ሁለት ጊዜ እየቆጠርክ/ሽ/ በመጨረሻም አንድ ጊዜ እየመታህ/ሽ/ ለመቀያየር ሞክር/ሪ/። (የx ምልክት የተቀመጠባቸው ክሮች በሙሉ ኮርዱን በምትጫወትበት/ቺበት/ ጊዜ አትነካቸውም/ኪያቸውም/።)

G C D7




እነዚህን ኮርዶች እላይ በተሰጠው መመሪያ መሰረት ከዚህ በታች ያለውን የቁጥር ልምምድ በመከተል ያለ መሰልቸት ተለማመድ/ጂ/ ።

↓= በአውራ ጣትህ/ሽ/ ወይንም በፒክ በትክክለኛው ቦታ ላይ ወደታች ተጫወት/ቺ/

↑ = በአመልካች ጣትህ/ሽ/ ወይንም በፒክ በትክክለኛው ቦታ ላይ ወደላይ ተጫወት/ቺ/



በዚህ የቁጥር ልምምድ ውስጥ ሁለት አይነት አመታት ትለማመዳለህ/ሽ/ አንደኛው በአውራ ጣትህ/ሽ/ አንድ ወደ ታች በአመልካች ጣትህ/ሽ/ አንድ ወደ ላይና ሁለተኛው በአውራ ጣትህ/ሽ/ አንድ ወደ ታች በአመልካች ጣትህ/ሽ/ ሁለት ወደ ላይ የምትጫወተው/ችው/ ሲሆን ልብ ልትል/ይ/ የሚገባው በአውራ ጣትህ/ሽ/ ምትጫወተው/ችው/ ዋናው ሪትም ላይ ሲሆን አመልካች ጣትህ/ሽ/ ደግሞ የሪትሙን ተቃራኒ ይጫወታል።

G C D7

1 2 3 4 1 2 3 4 1 2 3 4

↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑

G C D7

1 2 3 1 2 3 1 2 3

↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑

G C D7

1 2 1 2 1 2

↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑ ↓↑

G C D7

1 1 1

↓↑ ↓↑ ↓↑

G C D7

1 2 3 4 1 2 3 4 1 2 3 4

↓↑↑↓↑↑↓↑↑↓↑↑ ↓↑↑↓↑↑↓↑↑↓↑↑ ↓↑↑↓↑↑↓↑↑↓↑↑

G C D7

1 2 3 1 2 3 1 2 3

↓↑↑↓↑↑↓↑↑ ↓↑↑↓↑↑↓↑↑ ↓↑↑↓↑↑↓↑↑

G C D7

1 2 1 2 1 2

↓↑↑↓↑↑ ↓↑↑↓↑↑ ↓↑↑↓↑↑

G C D7

1 1 1

↓↑↑ ↓↑↑ ↓↑↑

ወደ መዝሙሩ ከመሄድህ /ሽ/ በፊት ከላይ ባየኸው/ሽው/ ምሳሌ መሠረት ሳትቸኩል/ይ/ በደንብ በቁጥሮች ተለማመድ/ጂ/ ጣቶችህ/ሽ/ በደንብ ከተፍታቱ ቀጥሎ ያሉትን መዝሙሮች ሳትጣደፍ/ፊ/ በዝግታ እየዘመርክ/ሽ/ በትክክለኛ ቦታ ላይ ኮርዶችን ለመቀየር ሞክር/ሪ/ መልካም ልምምድ ይሁንልህ/ሽ/ ።



# ምስጋና ምስጋና




## ሁሉም አለኝ






## አዩ ብቸኛው




D
G
A7
X X
X

# ተመስገን ነው


= 110
D
A7
ተ መስ ገን ነው ተ መስ ገን ነው ም
G
D
ና ለ ጌ ታ .. ችን ባንተ ያ ላ .. ለፍ ነው ባንተ
D
A7
Fine
G
1
2
ያ ላ ሽ ነፍ ነው ያ ላ ሽ ነፍ




D
ነው ዳ ገ ቱን ወ ጣ .. ነው እን
A7
D
ተ እየ መ .. ራ ኸን ቁል ቁ ለ ቱን
A7
ወ .. ረድን እን ተን ተ ከ .. ት ለን ይ
G
D
A7
ሂ ሁ ሉ ሲ .. ሆን ም ንም አል ተ .. ረ ታን
D
G
A7
D
D.c.
በ ድል ስ ላ ለፍ .. ነው እን በ ልሀ ተ መስ ገን

# ዘይትህን በመቅረዜ ሙላ









# ላይህ እናፍቃለሁ


♩= 94
ብር ሃ ንህ ብር ሃ ኔ ለ ኔ
ሆ ና .. በ መ ገ ዴ አን ተን እ ያ
የሁ ያ ወጅ ኩ ትን ሞ ት ሀን ቀ
ም ዬ .. በ ትን ሳ ኤ ል መ ስልህ እር
ዳኝ ላ ይህ እ ና ፍ ቃ ለሁ ጌ




ታ እና ፍ ቃ ለሁ ላ ይህ እ ና ፍ ቃ ለሁ ጌ ታ
ዬ የእ ጆ ች ህን ቁ ስል የእግ ር
ች ህን ቁ ስል የ ተ ወ ጋው የ ቀኝ ጎ ን ህን




# ድሉ የጌታችን ነው








# ስሙ ይክበርልን



♩= 100
A D A
ስ ሙ ይከ በ ር ልን .. ጌ ታ የ ሱስ
% D E7
የ ሰው ልጅ ፈ ጣ ሪ .. ያ ለም ን ጉስ
A D A
ስ ሙን እን ጠ ራ ለን .. በ ዕ ልል ታ
% E7 D A
አ ናፍ ርም በኢ የ ሱስ .. በ ኛ .. ጌ ታ
% D
እን ደ በት ተ ከፍ ቶ .. በ የዕ ለ
A % D
ቱ ፈ ጣ ሪ ውን ያከ ብር .. በ እው ነ







E7 A % D
ቱ ያ ለም ጥ በብ ጠፍ ቶ .. ከ ውስ ጣ
E7 D A
ችንኢ የ ሱስ ይከ በር .. በ ስ .. ጋ ችን

# እናምናለን በመስቀሉ









E
A
B7
X X
X
X

# ድንቅ ነው ለኔ ጌታ


♩= 84
E
B7
ድን ቅ ነው ለ ኔ ጌ .. ታ
E
ድን ቅ ነው ለ ኔ .. ኢየ ሱስ
B7
ሞ ኘነ ት ቢ መስ ላት ለዓ ለም




E
ድን ቅ ነው ለ ኔ .. ዘ ላ ለም
A
ግን በ ኞች የ ና ቁት .. .. የ ማ ዕ ዘን እ
E
B7
ራስ ለ ኔ ግን ድን ቅ ነው .. ..
E
ው ዱ ጌ ታ ኢ የ ሱስ ብ ዙዎች ያጥ ላ ሉ
A
E
ታል .. .. ር ካሽ እ ቃእ ድር ገው
A
B7
E
ለ ኔ ለ ደ ካ .. ማው .. .. ኢ የ ሱስ ድን ቅ ነው


# ለእግዚአብሔር እንቀኝ










# ኢየሩሳሌም


♩= 168
B7 E
የ ና .. ፈ ቀኝ ዜ .. ግ የ ት ..
B7 E B7 ٪
ዳስ ዝ ማ ሬ ዝ ማ ሬ አል ቀ
E B7 ٪ E
ርም ሳል ዘ ምር ከ ጳድ ታን አ ብ ሬ
B7 E
ከ በ .. ጉ ዙ ፋ ን ስር ሳል ዘ ..
B7 E B7
ምር በ ደስ ታ በ ደስ ታ


E B7 ٪
አል ቀ ርም ስ ላ ደሽ እን ቺ ት ድስት በ
E ٪ ٪
ታ ኢየ ሩ ሳ .. ሌም
٪ ٪ B7 E
ት ድስ ቲት ከ ተ ማ የ ጎ ዳ ናሽ ው
٪ ٪ A E
ጥን ት ጡ ቢ በ ዛ .. እንኳ ሳ ላ ደሽ አል ቀ
B7 ٪ E
ርም በእም ላክ ኃይል እር ዳ ታ




## ለእግዚአብሔር የሚሣን አለ ወይ ?








# ኑሮ ከጌታ ከየሱስ ጋር









# መንገዴን ሁሉ


መን ገ ዴን .. ሁ ሉ ጊ ታ ከ .. ተር
ጋር እስ ከ መ ጨ ረ ሻው ል ጓዝ
ል ሁን ካን .. ተ ጋር የ ዘ ላ ለም ሕይ
ወ ቴ ነህ መ ጠ ጊያ ና እምባ ዬ
እስ ከ ፍ ጻ ሜ እሄ ዳ ለሁ እን ተን ተ ከ .. ት
ዬ መን ገ ዴን ሁ ሉ ካን ተ ጋር




እስ ከ መ ጨ ረ ሻ እ ከ ተ .. ል
ሀ ለ ሁኝ .. .. የ ሕይ ወ ቴ .. ጋ ሻ




# አሸናፊ ነው ጌታዬ የሱስ

♩= 100








# ቀኑ ደርሷል



♩= 100
F
%
ቀ ኑ ደር ሷል ሊ ነ ፋ መ ለ ከት ሕዝብ
B♭
F
ይ ጠ ራል ካ ለ በት በ ፍጥ ነት ተ ሰብ ስ በን
C7
F
%
ልን ቆም በ ጊ ታ ፊት ታ ላ ቁ
%
%
ቀን ደር .. ሷል ኃ ይሉ የ .. ሚያ ስፈ ..
B♭
%
C7
ራ ም ድር ስ ት ና .. ወጥ ሊ
F
B♭
ሸ ሸን .. ተ ራ ራ የ ነ ገስ






C7
F
ታት ን .. ጉስ ሲ ገ ለጥ .. ክ ሰ ..
B♭
C7
F
ማይ በ ም ድር የ ቀ .. ሩት ይ
C7
F
ሉ ለ .. ታል ዋይ ዋይ


# ተመስገን ተመስገን







# ማይነር ኮርዶች

እስካሁን ድረስ የተጠቀምከባቸው/ሽባቸው/ ኮርዶች በሙሉ ሜጀር ኮርዶች ይባላሉ። ከዚህ ቀጥሎ የምትማረው/ሪው/ ማይነር ኮርዶችን ይሆናል። ሜጀር ኮርዶች ሁል ጊዜ በእንግሊዝኛ ትላልቅ(capital) ፊደላት ይጻፋሉ። ነገር ግን ማይነር ኮርዶች በእንግሊዝኛው ትላልቅ (capital) ፊደላት ከተጻፈ በኋላ ከፊት ለፊቱ የእንግሊዝኛውን ትንሿን (small) ኤም (m) ወይንም ትንሿን ኤም(m) እና አይ(i) ፊደላትን ከፊት ለፊቱ ያስከትላል። ለምሳሌ ያህል Am ፤Ami ፤Em ፤Emi . . .ወዘተ የሜጀርና የማይነር ኮርዶችን ቃና ለመለየት ተራ በተራ እየቀያየርክ/ሽ/ ለመጫወት ሞክር/ሪ/። ለምሳሌ G እና Em፤ C እናAm፤ F እና Dm፤ D እና Bm እነዚህን ኮርዶች እየቀያየርክ/ሽ/ ስትጫወት በሜጀርና በማይነር ኮርዶች መካከል ያለውን የድምጽ ልዩነት ልብ ለማለት ሞክር/ሪ/።እያንዳንዱ ሜጀር ኮርድ የራሱ የሆነ ተዛማጅ ማይነር ኮርድ አለው። ከታች የሚገኘው በስዕል መግለጫ ኮርዶቹ እንዴት እንደሚዛመዱ ያመለክታል።



ከዚህ በታች በማይነር ኮርዶች ላይ የተመሠረቱ መዝሙሮችን ታገኛለህ/ሽ/። ልክ በሜጀር ኮርዶች ላይ የተመሠረቱትን መዝሙሮች እንዳጠናኸው/ሽው/ ሁሉ ቀጥሎ በማይነር ኮርዶች ላይ የተመሠረቱትን መዝሙሮች በዝግታ እየዘመርክ/ሽ/ በትክክለኛ ቦታ ላይ ኮርዶችን ለመቀየር ሞክር/ሪ/።







# ዝናህ የገነነ



# ያዲስ ኪዳን በግ


♩= 110
ያ ዲስ ኪ ዳን .. በግ ቅ ዱስ ካ ህን
የ ጽድ ቅ ን .. ጉስ .. የ ዓ ለም መድ ኅን
የእው ነ ተ ኛ ይ ቱ ድን ኪን አ ገል ጋይ
ቅ ዱስ ካ ህን እ ለን .. በ ላይ .. በ ሰ .. ማይ
ክብ ዶን የ ነ በ ረ .. የ ሕ .. ግ ጭ ነት
ፍጥ ረ ትን ሲያስ ጨ ንቅ .. ስ ለ ኃ ጢ አት





የ ሕዝ ብን ኃ ጢ አት .. እን ዴ .. ለ ማስ ተ ረት
የ ሱስ ሕይወ ቱን ሰ ጠ .. በ መስ ቀል ስ ቅ ላት

# ክብር ይገባሃል


= 110
Em Bm
ክ ብር ይ ገ ባ ሃል .. የ ኛ አምላክ
Em Am
ክ ብር ይ ገ ባ ሃ .. የ ኛ አምላክ
Bm Em
ዙ ፋ ንም ምስ ጋ ናም ላን ተ ነው
Bm Em
ዙ ፋ ንም ምስ ጋ ናም ላን ተ ነው
Bm Em Am
ክ ብር ሃ ሌ ሉ .. ያ ክ ብር ሃ ሌ ሉ .. ያ
Em Bm Em Am
ክ ብር ሃ ሌ ሉ .. ያ ክ ብር ሃ





Em
ሌ ሉ ያ ዘ ላ ለ ማዊ አም ላክ ..
Bm Em
አን ተ ነህ ዘ ግ ጅ ነው ክ ጥንት ..
Am Bm Em
ዙ ፋ ንህ ወን ዞች ከፍ አ ረ ጉ ድም ጸ ቸ ውን
Bm Em
ተ ራ ሮ ችም ጤ ሱ ስ ጡ ክብ ርን


Am
Dm
Em
X
X X


# አንተ ታላቅ ነህ


♩= 110
Em
በ ዘ መ ና ችን በ
Am Em
ዓ ለም ሁ ሉ .. ከ ቁ ጥር በ ላይ
Dm
.. .. አ ማ ልክት አ ሉ .. ተ
Am Dm
ወ ዳ ዳ ሪ እ ቻ የ ሌ ለህ ..




Em Dm
እው ነ ተ ኛአም ላክ አን ተ ብ ቻ ነህ
Am Em
.. አን ተ ታ ላቅ ነህ ለ
Am Em
ዘ ለ ዓ ለም እን ዳን ተ ያ ለ
Dm
ድንቅ አም ላክ የ ለም .. ት
Am Dm
ልቅ እ ድል ነው ባን ተ መ ጠ ራት ..
Em Dm Am
በአ ህ ዛብ መ ኻል .. .. ሥ ራ ህን ማው ራት ..

# ክብር ክብር


= 86
Dm Am
ክ ብር ክ ብር ክ ብር ክ ብር ክ ብር ክ
Dm Am Dm
ብር ጊ ታ ለእን ተ . .. ይ ሁን ..
Am Dm
በ ሰ ማይ በ ም ድር መ ካ ኒ ቱን በ
Am Dm
ልጅ .. የ ባ ረ ካት .. ደስ የ ተ ሰ ኘች
Dm Am Em
ሴት .. ያ ደሰ ረ ካት .. ምስ ኪ ኑን ክ አ





Am Dm Em
መድ ያ ነ ሳ ኸው ለ ሹ መት ሽ ል
Am Dm Em Am
ማት .. ያ በ .. ቃ ኸው.. ክ ብር ላን ተ .. ይ ሁን

# ምስጋናዬ ከፍ ብሏል



♩= 164
Am Em Dm
ነ ገስ ታት ኃ ያ ላን .. .. አ ለ
ቆች .. .. በ ሙ ሉ እግ ዚአ ብሔር ታ ላ
ቅነው .. .. ት ዱስ ነው .. ይ በ ሉ ..
አ ቻም በ አት ማ ችን .. .. ሥ ራ
ህን .. .. አይ ተ ናል ግ ሩም ነህ ድን ቅ
ነህ .. .. ተ መስ ገን .. ብ ለ ናል ..
ምስ ጋ ና ዬ




ከ ፍ ብ ሏል .. በ ፊ ት
ህ ምስ ጋ ና
ዬ ከ ፍ ብ ሏል ..
በ ፊ ት ህ
እግ ዚአ ብሔር ሆይ አ ቻም የ ለ
ህም .. ም . ..
የ ኔ ጌ ታ ወ ደር የ ለ
ህም ም .. ም


Bm
Em
F#m
x x
x x

# አንተ ብቻ ነህ


= 156
Bm
Em Bm
አን ተ ብ ቻ ነ ሀ አን ተ ብ ቻ ነ
F#m
Bm
ሀ አን ተ ብ ቻ ነ ሀ ጌ ታ አን ተ ብ ቻ ነ
Bm F#m Bm
ሀ አን ቆ ቅ ል ሽን .. የ ም ት ፈ ታ





F#m Bm
.. ጨ ለ ማ ው ንም .. የ ም ት በ ራ
Em F#m Bm
.. ማ ሀ ተ ሙ ንም .. የ ም ት ፈ ታ
F#m Bm
.. አን ተ ብ ቻ ነ ሀ ጌ ታ አን ተ ብ ቻ ነሀ ..

# የኃያላን ኃያል


♩= 156
Bm F#m Em
ብ ዙ ኃ ያ ላ ኖች .. በም
Em Bm
ድር ላይ ነ በ ሩ በእን ድ ዘ መን ታይ
F#m Bm
ተው .. ጠፍ ተው በ ዚያው ቀ ሩ የ
Em
ኖ ኢ የ ሱስ ግን .. መ ቃ ብር ፈን
Bm
ቅ ሎ ከ በ ረ በ ሰ ማ ይ እ ሚን
F#m Bm
በ ሞት ላይ እ ይሎ የ ኃ ያ ላን ኃ





ያል የ ኖ ጌ ታ በ ሰ ልፍም እ ጅ
Em
ጉን የ በ ረ ታ እን ደ እርሱ የ ሚ
F#m Bm
ሆን ማ ንም የ ለም .. .. ከ በር .. .. ን
ገስ ለ ዘ ላ ለም ..


= 156
F#m Bm Em Bm F#m
በ ምስ ጋ ና ዝ መ ቱ በ ምስ ጋ
Bm Em F#m Bm
ና ዛ ሬ .. በ ምስ ጋ ና
Em Bm F#m Bm
ተ ቀ ጉ በ ዝ ማ ሬ
እስ ራ ኤል ለ ው ጊያ ጠ ር ነት ሲ ወ
Em Bm
ጣ ጠ ላ ትም በ ትም ክህት ሲ ፎ ክር ሲ መ
Em Bm
ጣ ይ ሁ ዳም .. እም ላ ኩን ..




Em Bm
ማ መስ ገን ሲ ጀ ምር .. .. እግ ዚእ
F#m
ብሔር እስ ነ ሳ ድ ብት ጦር




# የአምላክ ዋጋው ምስጋና ነው









# አቤቱ ጉልበቴ ሆይ







# ይብዛልህ እንጂ ምስጋና









## <u>ጣቶችህን/ሽን/ በማንሸራተት ልትጫወት/ቺ/ የምትችላቸው/ያቸው/ ኮርዶች</u>


## <u>( Close position )</u>

ከፍሬት ወደ ፍሬት በማንሸራተት ልትጫወታቸው/ቺያቸው/ የምትችልባቸው/ይባቸው/ ዝግ ( <u>Close position</u> ) ኮርዶች አሉ። ለምሳሌ ያህል F ኮርድን ይዘህ/ሽ/ ጣቶችህን/ሽን/ ሳትነቅል/ይ/ ወደ ሶስተኛው ፍሬት ዝቅ ብትል/ይ/ G ሜጀር ኮርድን ታገኛለህ/ሽ/። እንዲሁም ወደ አምስተኛው ፍሬት ዝቅ ብትል/ይ/ A ሜጀር ኮርድን ታገኛለህ/ሽ/። በዚህ ዓይነት ከፍሬት ወደ ፍሬት በመንሸራተት በርካታ የተለያዩ ኮርዶችን ማግኘት ትችላለህ/ሽ/።

F





B♭








F





B♭




Dm





Fm7




Dm




Fm7








## ባሬ ኮርድ


ባሬ ኮርድ በአመልካች ጣቶችህ/ሽ/ ስድስቱንም ክሮች በመያዝ የምትጫወተው/ቺው/ የኮርድ ዓይነት ነው። ይህን ኮርድ ጣቶችህ/ሽ/ በደንብ ከለመደው ውብ የሆነ የተሟላ ሕብረ ድምፅ ታገኛለህ/ሽ/። በመጀመሪያ እነዚህን ኮርዶች ማጥናትና መጫወት አስቸጋሪ መስሎ ይታያል። ሆኖም ለጥቂት ሳምንታት ያለ መሰልቸት ተለማመድ/ጂ/። በመጨረሻም ጣቶችህ/ሽ/ ይሰለጥኑና የምትፈልገውን/ጊውን/ የባሬ ኮርዶች መጫወት የምትችልበት/ይበት/ ደረጃ ላይ ትደርሳለህ/ሽ/።


አንዳንድ ጊዜ የጊታር ተማሪ የባሬ ኮርድን ጊዜ ወስዶ/ዳ/ ከማጥናትና ከመልመድ ይልቅ በካፖ መጫወትን ይመርጣል/ትመርጣለች/። ይህ ሁኔታ ግን በጊታር ላይ ልትለምድ/ጂ/ የምትችላቸውን/ያቸውን/ የጣት ቴክኒኮች እና የጣት ፍጥነትህ/ሽ/ እንዳይጎለብት ተጽእኖ ያሳድራል። በተቻለ መጠን በካፖ ላለመጠቀም ሞክር/ሪ/።


በተለይ በኤሌክትሪክ ጊታር ላይ ካፖን አትጠቀም/ሚ/። ኤሌክትሪክ ባልሆነ/ሽበ ወይንም ናይለን/ ጊታር ላይ በካፖ እንድትጠቀም/ሚ/ የሚያስገድድህ/ሽ/ ሁኔታ ከተፈጠረ ከአምስተኛው ፍሬት በታች ካፖውን አትሰር/ሪ/። ያለ ካፖ መጫወት ግን በጊታር አጨዋወትህ/ሽ/ ላይ ረቀቅ ያለ ችሎታ እንዳለህ/ሽ/ ያሳያል።

















## ድብልቅ /ማይነር ፥ ሜጀር/ ኮርዶች አጠቃቀም

እስካሁን ድረስ በተነጣጠለ ሁኔታ በሜጀርና በማይነር ኮርዶች ላይ ብቻ የተመሠረቱ መዝሙራትን ተመልክተሃል/ሻል/። ነገር ግን በአንድ መዝሙር ውስጥ ሜጀርንም ሆነ ማይነር ኮርዶችን በማደባለቅ መዝሙሩን ማጀብ ይቻላል። እያንዳንዱ ሜጀር ኮርድ የራሱ የሆነ ተዛማጅ ማይነር ኮርድ አለው። በገጽ <u>45</u> ላይ ያለው ስዕል ምን ሜጀር ኮርድ ከምን ማይነር ኮርድ ጋር ተዛማጅ እንደሆነ ያሳያል። ለምሳሌ ያህል C ከ Am፤ G ከ Em፤ D ከ Bm . . . ወዘተ ።


አንድ በ D ሜጀር ላይ የተመሠረተ መዝሙር ስትጫወት/ቺ/ G እና A7 ኮርዶችን በተቀጽላነት ወይም በአጫፋሪነት ትጠቀምባቸዋለህ/ሽ/። ሆኖም በG እና በA7 ኮርዶች ፈንታ Em እና F#m ኮርዶችን መጠቀም ይቻላል። ለዚህም ምክኒያቱ Em የG እንዲሁም F#m የA ተዛማጅ ኮርዶች ስለሆኑ ነው። በእንደዚህ አይነት የተደባለቁ ኮርዶች ላይ የተመሠረቱ መዝሙሮች ሲያጋጥሙህ/ሽ/ ለጆሮህ/ሽ/ በሚጥሙና ለመዝሙሩ በሚስማማ መልኩ የተለያዩ ኮርዶችን ተጠቀም/ሚ/። ሆኖም የምትመርጣቸው/ጫቸው/ ኮርዶች ላይ ባየነው ምሳሌ መሠረት ምን ያህል ኮርዶቹ እርስ በእርሳቸው ተዛማጅ እንደሆኑ እርግጠኛ ሁን/ኚ/።

# ብርሀን አየሁ






# ና ወደኛ



# ካልባረከኝ






# አለኝታዬ



# ሽክም ይሰማሃል ወይ




ሽ ክም ይ ሰ ማ .. ሃል ወይ .. ክ ርስ
ቲያን ወን ድ ሟ ሆይ ለ ሚ ጠ ፋት ወ .. ገ
ኖች .. ል ብህ ያ ዝን ብ .. ሀል ወይ ጥ ፋ
ታ ቸው ተ .. ሰም ተህ .. አዝ ነህ ት ጸ ል ያ
ለህ በ ራ ስህ ተ መ .. ክ ተህ .. ወ ይስ






በ መፍ ረድ .. ላይ ነህ በ ሞት
ጎ ዳ ና .. ላይ ሆ ነው ወ ደ ሞት ሲ ያ ዘግ
ሙ ል ብ ህስ ያዝ ን .. ብ ሀል ወይ ይ ሰ
ማ ሀል ወይ .. ሽክ ሙ

# ቃልህን ለማንበብ


♩= 168
E7 F#m A
ቃ ልህን ለ ማን በብ ጓይ ኔ
F#m A D
ታ .. ወ ሬ ላል ጸ ልይ ጉል በ ቴ
E7 Bm D
ታ ሰ ሬ እን ተን እን ዳ ላ ሰብ
A E A E7
አእም ሮ ዬ ዛ ለ እግ ሬም
F#m A
ወ ደ ጥ ፋት ኮ በ ለ ለ እ ኔን




E F#m D E7
ጊ .. ታ ሆይ ድ ካም ይ .. ዞ ኛል
A F# Bm
ድም ፄ ንም ላ ሰ ማህ እ ቶ ቶ ኛል
E7 A D
ወ ድ ቁአ .. ለ ሁኝ ጊ ታ
A E
ሆይ .. እን ሳኝ እ ባ ክህ ሕይ ወ
A E7 A
ቱን ለ ው ጥ ልኝ

# ይመስገን ጌታ ይመስገን








# ግሩም ነው ድንቅ ነው


♩= 100
B♭ Cm7
ግ ሩም ነው ድን ቅ ነው ገ ታ ሲ ስ
Dm7 E♭
ራ እ የ ነው ምር ኮው ላይ ግር ማው ሲያ በ
Dm7 B♭
ራ የጋ ጢአት መ ጋ ረ ጃን በ ደ ሙ ቀ
Cm Dm Gm E♭
ደ ደ ከ ሳ ሳ ችን አፍ ር ወድ ቆ ሰ ገ
B♭ Dm7 B♭
ደ ዶ ከ ሰን የ ነ በ ረው የ ዕ ዳ ጽ





Cm Dm7 Gm E♭
ሕ ፈት በ ደ ሙ ተ ደ ምስ ሷል በ ጌ ታ ኢየ ሱስ
B♭ Dm7
ሞት ቀ ን በ ራ ችን ተሰ ብሯል አ ር
B♭ Cm Dm7
ነት ወ ጥተ ናል ጠ ላ ቶች የ ነ
Gm E♭ B♭
በር ነው በ ጸ ጋው ቀ ርበ ናል

# ጌታ አምላካችን


♩= 90
Dm B♭ Dm F
ጌ ታአም ላ ካ ችን እን ተ ሥ ራ በት
Dm E♭ Cm7
በ ኃ ያል ክን ድህ ተ መ ላ ለ ስ በት .. ..
Dm E♭ Gm
ጎስ ቋ ላ ነ ታ ችንን በ ደ ምህ ሽ
B♭ Dm
.. ፍ ነህ በ ዚህ ስፍ ራ ክ በር ስ ለ ስ
B♭ Fine Dm E♭
ምህ ክፍ ይ በል ጌ ታ ችን ክ




Gm B♭ Dm E
ብርሀ ያስ ተ .. ጋ ባ ቀ ድ ስን በ ደ ምህ
B♭ Cm Dm
ራይ ህን ስብ ሰ ባ .. .. ታ ላ ቅ ነት
E♭ Dm E♭
ህን እ ን የው እ ባ ክህ አብ ራ መብ ራ
Dm Cm B♭ D.C.
ት ህን .. .. ያን ጸ ባርቅ ሞ ገ .. ስህ

# አዲስ ሰው ሆንኩኝ


♩= 90
Em
አ ዲስ ሰው ሆን ኩኝ .. አ ዲስ ፍጥ ረት ከ
CM7 D Em
ቶ ላይ ገ ዛኝ .. ኃ ጢአት ወ ይም ሞት
ክ ማይ ጠ ፋ ዘር ተ
Am
ወ .. ል ጄ ለሁ በእግ
CM7 D Em
ዚአ ብሔር መን ፈስ ተ ለ ው ጫ ለሁ





እን ደ ል ጅም እ
Am
ኔም .. አድ ጋ ለሁ እን
CM7 Bm D Em
ዲ ሁ እንዳል ቀር ተ ረ ድ ቻ ለሁ

# መሸሸጊያ ዋሻ


♩= 110
Em GM7
መ ሸ ሸ ጊ ያ ዋ ሻ መ
Bm Em Am7
ሸ ሸ ጊ ያ ዋ .. ሻ መ ከ ታ ጋ ሻ ችን መ
Em GM7
ከ ታ ጋ ሻ .. ችን ጠ ራ ችን እን ተው ነህ ጠ
Em Am7
ራ ችን እን ተው .. ነህ ጠ ላ ትን መው ጊያ .. ችን ጠ
Em7 GM7
ላ ትን መው ጊያ .. ችን እን ተም ተ ዋ ጊ ነህ ስ
Em7 Am7 G C
ምህ እግ ዚአ ብሔር ነው እን ኮ ራ ብ ሃ ለን ደስ




D Em
ታህ ኃይ ላ ችን ነው ክ
GM7
ግብ ጽ ባ ር ነት ከ ፈ ር እን ግ ዛት ብ
Bm C D
ር ሃን ጨ ለ ሞ ሞት በ ስ ፈ ነ በት ል
Em GM7
ጆ ችህ ሲ ጮ ኹ ባ ር ነት መ ሯ ቸው እን
Bm C D
ተ ነህ ተ ዋግ ተህ ነ ጻ ያ ወ ጣ ሃ ቸው እን
Bm C D Em
ተ ነህ ተ ዋግ ተህ ነ ጻ ያ ወ ጣ ሃ ቸው

# ወንጌላችን ገና ድል ያደርጋል









# ኑሮህና ጊዜው


♩= 84
Bm
Bm7
ኑ ሮ ህ ና ጊ ዜው ባይ ሆን ም ቾ
G
A
ጠ ላ ቶች ቢ በ ዙ ቢ ከ ፃ .. ቾ
Bm
Bm7
ጊ ታእን ተን ሊ ረ ዳ በ መ ከ ራ
G
A
F#m
Bm
እ ለ ካን ተ ጋ ራ
D
Bm
በ ሕይ ወት ዘ መ ንህ ች ግር በ ዝቶ




G
Bm
ኑ ሮ ህም ቢ መ ርህ ተ በ ላሸ ቶ
A
D
ጊ ታ ይ ረ ዳ ሀል ቁም ተጽ ና ና
A
Bm
ወ ደ ሰ ማይ ቢ ትህ እስ ኪ ልሀ ና

# አቤቱ እናመሰግንሀለን








# እንደ ተቀበልኩት ምህረት








# በእርግጥ ጌታ



♩= 176
Dm Am7
በር ግጥ ጌ ታ ከ ኛ ጋር .. ባይ ሆን ..
Dm Gm Am
እር ሱ ባ ይ ዋ ጋ ልን .. .. ..
Dm Am7 C
የ ጠ ላ ታ ችን ሰልፍ አ .. ይ ሎ ..
Dm Am Dm %
ከ ም ድር ላይ በ ጠ ፋን ስ ለ ዚህ ስ ለ
C F
ዚህ እግ ዚአ ብሔር ይ መስ ገን ስ ለ






Dm Gm %
ሁ ሉም ነ ገር የእ ሳት ሰ ረ ገ ላ .. .. ብር ቱ
% %
ሰልፍ ከ በ .. ናል ከ ኛ ጋ ራ ያ
% % Dm
ሰው .. .. ከ ሁ ሉም ይ በ .. ጣል መ ለ
Am Gm Dm
ከ ትን ን ፉ ጠ ላት ይ ታ ወ ራል ብ ቃ
% Am Dm
እምነት ይ ኑ ረን ኢየ ሱስ ያ ሸ ን ፋል

# አንድ ነን በመንፈሱ






እስካሁን ድረስ ልብ ብለህ/ሽ/ ከሆነ የተጫወትካቸው/ሻቸው/ መዝሙሮች ሁሉ የሚያልቁት በተመሠረቱበት ዋና ስኬል (scale) የመጀመሪያው ድምፅ ላይ ነው። (ስለ ስኬል (scale) የተሠጠውን መግለጫ በገጽ <u>148</u> ላይ ተመልከት/ቺ/)። ለምሳሌ ያህል የገጽ <u>13</u> መዝሙር <u>ምስጋና ምስጋና</u> በG ሜጀር ስኬል ላይ የተመሠረተ ነው። መዝሙሩም ያለቀው በዛው በG ሜጀር ስኬል ላይ በሚገኝ ድምፅ (tone) ላይ ነው። ነገር ግን አንዳንድ መዝሙሮች በተመሠረቱበት ዋና ሜጀር ወይም ማይነር ስኬል ውስጥ ሆነው እያሉ የሚያበቁት ግን ስኬሉ በተመሠረተበት ዋና ድምፅ ላይ ሳይሆን በሁለተኛው ወይም በአምስተኛው ድምፅ (tone) ላይ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል የገጽ <u>116</u> መዝሙር <u>ምስጋና ምስጋና ክብር</u> የተመሠረተው በD ሜጀር ስኬል ላይ ሆኖ እያለ መዝሙሩ ግን ያበቃው በስኬሉ አምስተኛው ድምፅ ማለትም በA ድምፅ ላይ ነው። ይህ ማለት ግን መዝሙሩ በA ሜጀር ስኬል ላይ የተመሠረተ ነው ማለት አይደለም።

አንዳንድ ሰዎች በዘልማድ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚያልቁ መዝሙሮችን ደስታ ስኬል ወይም ግልብጥ ስኬልና ሌላም የተለያዩ ስሞችን ሲጠቀሙ ይታያል። ነገር ግን በሙዚቃው ዓለም እነዚህ አባባሎች ትርጉም ካለመስጠታቸውም በላይ ተቀባይነት የላቸውም።

ሌሎች ደግሞ መዝሙሩ የተመሰረተበትን ስኬል መነሻ በማድረግና መዝሙሩ የጨረሰበትን ድምጽ በማገናዘብ የተለያዩ ስያሜዎችን ይስጧቸዋል። ለምሳሌ በC ስኬል ላይ ተመስርቶ ፣ ያበቃው ግን በስኬሉ ሁለተኛ ድምጽ ላይ ከሆነ በመጨረሻ የምትይዘው/ዢ/ ኮርድ Dm ይሆናል። ስለዚህም መዝሙሩን C ሜጀር ሰከንድ ( C 2nd ) ይሉታል። እንዲሁም በC ስኬል ላይ ተመስርቶ ያበቃው ግን በ ስኬሉ አምስተኛው ድምጽ ላይ ከሆነ በመጨረሻ የምትይዘው/ዢ/ ኮርድ G ሜጀር ይሆናል። ስለዚህም መዝሙሩን C ሜጀር ፊፍዝ ( C 5th ) ይሉታል።

ሌሎች ደግሞ ማንኛውም ስኬል በራሱ ሙሉ ሆኖ ይጠራል እንጂ በሌላ ስኬል ላይ ተደግፎ መሰየም የለበትም ይላሉ። ለምሳሌ ያህል C ሜጀርና A ማይነር ናቹራል ስኬል አንድ አይነት የድምፅ ግንባታ ይጠቀማሉ። ነገር ግን መዝሙሩ በ A ላይ ቢያበቃ A ማይነር እንጂ C ሜጀር ሲክስ ( C 6[th]) ተብሎ አይጠራም። በዚሁ ቲዎሪ መሰረት በC ስኬል ላይ ተመስርቶ ያበቃው ግን በስኬሉ ሁለተኛ ድምጽ ላይ ከሆነ በመጨረሻ የምትይዘው/ዢ/ ኮርድ Dm ይሆናል።

ስለዚህም መዝሙሩ D ዶሪያን ( Dorian ) ብለው ይጠሩታል። እንዲሁም በC ስኬል ላይ ተመስርቶ ያበቃው ግን በስኬሉ አምስተኛው ድምጽ ላይ ከሆነ በመጨረሻ የምትይዘው/ዢ/ ኮርድ G ሜጀር ይሆናል። ስለዚህ መዝሙሩን G ሚክሶሊዲያን (Mixolydian ) ብለው ይጠሩታል ። በሶስትኛው ድምፅ ላይ ካለቀ ፍሪጂያን ( Phrygian ) ፤ በአራተኛው ድምፅ ላይ ካለቀ ሊዲያን (Lydian ) ፤ በስድስተኛው ድምፅ ላይ ካለቀ ኤዎሊያን ( Aeolian ) ፤ በሰባተኛው ድምፅ ላይ ካለቀ ሎኒያን (Lonian ) ብለው ይጠሯችዋል።

ሌሎች ደግሞ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ለሚያልቁ ዜማዎች ሃገራዊ የሆኑ ማለትም እንደ ትዝታ ባቲ ወዘተ የመሳሰሉ ስያሜዎችን መስጠት ይገባናል ይላሉ።

ከላይ በግልጽ ለማሳየት እንደተሞከረው በጣም የተለያዩ ስያሜዎች፣ አመለካከቶችና ቲዎሪዎች በነዚህ ስኬሎች ዙሪያ በሙዚቀኞች አካባቢ ይገኛሉ። ጉዳዩ በጥልቀት ጥናት የሚያስፈልገው ሆኖ ስላገኘነውና ጥናትም እየተደረገበት ስለሆነ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በነዚህ ስኬሎች ላይ ለተመሰረቱ መዝሙሮች ግልፅ የሆነ ስያሜ ከመስጠት ተቆጥበናል።



# አቤት እግዚአብሔር



# ምን እሆናለሁ



♩= 156
E F#m A
ም ድር ስ ት ጨ ነት .. ዘ መ
Bm7
ኑ ሲ ከ ፋ .. .. .. .. .. እ ኔእን
A F#m Dm
ተን ይ ዣ ለሁ የ ዘ ላ ለም ተስ ፋ
E F#m Bm
.. በ ቤ ትህ እ ለ ሁኝ .. እስ ካ
ሁን ተ ጉ ዤ .. .. .. .. እ የ





F#m Dm
ዘ ማ መር ኩኝ በ ገ ና ዬን ይዤ ..
E A
.. ምን እ ሆ ና ለሁ ጌ ታ
F#m A' D A
ምን እ ሆ ና ለሁ .. .. ምን እ ሆ ና ለሁ
E
እን ተን እ ግኝ ቻ ለሁ .. ..

# መፈታቴን አውጃለሁ

♩= 150






# እንደ ማርያም ልሁን


♩= 110
G Am Bm7
እን ደ ማ ርያም ል.. ሁን .. .. ል ወ ትህ ለ ይ
Am G Am
ቺ የ ከ በ ረውን ሽ.. ተ .. ..
Bm7 Am G
በ ፊ ትህ አፍ ስ ሼ ስ ዎ ችን ሳል ፌ..
Am Bm7 Am
ራ .. .. ይ ሉኝ ታም ሳ ይ ዘኝ
G Bm7 Am
በ ፊ ትህ ቆ ሚያ ለሁ ል ጄ ማር ኩህ(ሽ) በ ለኝ




Em Am GM7
የ ተ ደ ቆ ሰ ልብ .. .. ስ ጠኝ የ ደ ቀ
Am Em Am
ቀ የ ሚ ቀ ረኝ አይ ኑር .. ..
GM7 Am Em
ከንተ የ ተ ደ በ ቀ ዝ ቅ ብ ዬ አ
Am GM7 Am
ግርሀን .. .. በአን ባ ዬ ላ ር ሰው
GM7 Em Am
ልስ በ ረው ጠር ሙ ሉን በ ፊ ትህ ላፍ ስ ሰው


# ምስጋና ምስጋና ክብር








# አንተ ምስጋናዬ ነህ


♩= 150
D Em
አን ተ ምስ ጋ ና ዬ ነህ አን
F#m Bm D
ተ ምስ ጋ ና ዬ .. ነህ አን ተ ምስ ጋ ና
Bm A Em7 Bm
ዬ ነህ በ ዓ መ ታት .. .. .. ከ
Bm7 Em7
ቶ ሲ መ ጣ .. ያ መ ለጥ ኩ ብህ
Em Bm7 Bm
.. ስ ጣል ስ ሬ ሳ .. የ




Em
ታ ቀፍ .. ኩ ብህ .. ባን ተ እዚህ ደ ረስኩ
Bm Em
.. ክ ኔ ጋር ሆ ነህ .. ኢ
Bm
የ ሱስ ለ ኔ .. .. ምስ
Em
ጋ ና ዬ ነህ ..

# ክብር ለሆነን ጌታ


♩= 150
B E
ክ ብር ለ ሆ ነን ጌ ታ ሞ ገስ
G#m C#m F#m
ለ ሆ ነን ጌ ታ ብ ቃት ለ ሆ ነን ጌ
A B
ታ በ ጉድ ለ ታ ችን ፈን ታ ክን ዱን
E G#m
በ ዘ መ ና ችን በአይ ና ችን አይ ተ ነ
C#m F#m
ዋል መል ካ ሙእ ረ ኛ ኢየ ሱስ እስ ከ
A B C#m
ዛ ሬ ረድ ቶ ናል በ ዘ መን ባ መ





A B
ታት መ ሃል .. የ ሚ ገ ዳ ደ ረው የ ታል ብ
C#m A
ቻ ውን ድንቅ እ የ ሠ ራ .. የ ሚ ኖር እን ደ
B EM7
ተ ፈ ራ ለ እኛም ይ ኸው ሞ ገስ ሆ ነን ባ
C#m EM7 B
ሀ ሩን ከፍ ሎአ ሽ ገ ረን ች ግ ራ ች ንን
A B
ረ ሳ ነው በኢ የ ሱስ ስን ቱን አ ለፍ ነው

# ጌታ ለኛ ያረገው



= 110
F#m
የ ማ ይ ቻ ለው .. በ
EM7
C#m
ር ሱ ተ ችሎ ሲ ዝት ሲ ፎ ክር .. ስን
F#m
ቱ ተ ጥ ሎ በ ሚያ በ ረ ታው .. ጌ
EM7
C#m
ታ በር ት ተን እ ዚህ ደር ሰ ናል .. ሁ
F#m
ሉ ንም አል ፈን ጌ ታ ጌ ታ ለ




F#m
C#m
Em
ኛ ያ ረ ገው .. .. እ ጅግ ብ ዙ ነው ..
F#m
እ ቤት እ ቤት ስን ቱን እ ለፍ ነው
C#m
F#m
.. .. በር ሱ ች ለ ነው .. ብር
C#m
F#m
B
ታት ብር ታት ጉል በት ሆ ነ ልን ..
EM7
C#m
F#m
ስ ሙ ስ ሙ ከፍ ይ በ ል ልን ..


## ተጨማሪ ኮርዶች

| Major (M) | 6th | Dominant 7 ( 7) | (9th) |
|---|---|---|---|







| Minor (m) | Minor 6th (m6th) | Minor 7 (m7) | Minor 9th (m9th) |
|---|---|---|---|




Major | (6th) | Dominant 7 | (9th)







Minor (m) | Minor 6 m6 | Minor 7 (m7) | Minor 9 (m9)




Major 7 (M7) | Major 9th (M9) | Major 11 (M11) | ( 13)







Diminished 7 (dim7) or (o) | Augmented (+) | Suspended 4 (sus 4) | 7 Suspended 4 (7sus4)




Major (M) | 6th | Dominant 7 7) | (9th)






Minor (m) | Minor 6th (m6th) | Minor 7 (m7) | Minor 9th (m9th)



# <u>ሙዚቃን ማንበብ</u>


በዓለም ላይ የሚገኙ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚጻፉበትና የሚነበቡበት የራሳቸው የሆነ ፊደላት አሉአቸው። እንዲሁም ሙዚቃ የራሱ የሆነ የሚጻፍበትና የሚነበብበት ምልክቶች አሉት። እነዚህም ምልክቶች በሁለት ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ።

እነርሱም :-

1. <u>Duration</u> (የቆይታ ግዜ) የድምፅን ርዝመትና እጥረት የምንገልጽበት
2. <u>Pitch</u> (የድምፅን ከፍተኛነት ወይም ዝቅተኛነት) የምንገልጽበት ናቸው።

1. <u>Duration</u> (የቆይታ ግዜ)

እያንዳንዱ በዜማ ውስጥ የሚገኝ ድምፅ የየራሱ የሆነ የጊዜ መጠን አለው። ስለሆነም የአንዱን ድምጽ የጊዜ መጠን ከሌላኛው ድምፅ የጊዜ መጠን ለመለየት የተለያዩ የኖታ ምልክቶችን እንጠቀማለን። ኖታ ከታች በስእሉ እንደተገለጸው ሦስት የተለያዩ ክፍሎች አሉት።






## <u>የኖታ የቆይታ ጊዜዎች</u>

𝅝 1 Whole-note (ሙሉ ኖት) 4 Beat (አራት ምት)

𝅗𝅥 2 Half-notes (ግማሽ ኖት) 2 Beat (ሁለት ምት)


♩ 4 Quarter-notes (ሩብ ኖት) 1 Beat (አንድ ምት)

♪ 8 Eighth-notes (ስምንተኛ ኖት) 1/8 Beat (ግማሽ ምት)

𝅘𝅥𝅯 16 sixteenth-note (አስራስድስተኛ ኖት) 1/16 Beat (ሩብ ምት)

ሁለት Eighth-notes (ስምንተኛ ኖት) በ ♪ ♪ ወይም ♫ ዓይነት ሊጻፍ ይችላል።

እንዲሁም sixteenth-note (አስራ ስድስተኛ ኖት) 𝅘𝅥𝅯 𝅘𝅥𝅯 𝅘𝅥𝅯 𝅘𝅥𝅯 ወይም 𝅘𝅥𝅯𝅘𝅥𝅯𝅘𝅥𝅯𝅘𝅥𝅯 ሊጻፍ ይችላል። የኖታዎቹ ዘንግ ደግሞ በ 𝅗𝅥 𝅗𝅥 𝅘𝅥 𝅘𝅥 𝅘𝅥𝅮 𝅘𝅥𝅮 𝅘𝅥𝅯 𝅘𝅥𝅯 መልኩ ሊጻፍ ይችላል።





<u>Rests (እረፍት)</u>

በዜማ ሂደት ውስጥ ድምፅ የሚሰማባቸውና የማይሰማባቸው ሂደቶች አሉ። ድምፅ በሚሰማባቸው ጊዜያት ኖታዎችን የምንጠቀም ሲሆን በዚያው አንጻር ደግሞ ድምፅ የማይሰማባቸው ጊዜያቶች ሲኖሩ ደግሞ የተለያዩ የእረፍት ምልክቶችን እናገኛለን።


𝄻 1 Whole-rest (ሙሉ እረፍት) 4 Beat (አራት ምት)

𝄼 2 Half-rest (ግማሽ እረፍት) 2 Beat (ሁለት ምት)

𝄽 4 Quarter- rest (ሩብ እረፍት) 1 Beat (አንድ ምት)

𝄾 8 Eighth- rest (ስምንተኛ እረፍት) 1/8 Beat (ግማሽ ምት)

𝄿 16 sixteenth-rest (አስራ ስድስተኛ እረፍት) 1/16 Beat (ሩብ ምት)



<u>Time signature(የጊዜ መለኪያ)</u>

ማንኛውንም ዜማ ስንጫወት ሆነ ስንሰማ የራሱ የሆነ የጊዜ ፍጥነት አለው። ይህም Pulse(ትርታ) ወይም Beat(ምት) ተብሎ ይጠራል። በዜማው ውስጥ አንዱ Beat(ምት) ከሌላው Beat(ምት) ጠንከር ያለ ሆኖ እናገኘዋለን ሁል ጊዜ ጠንከር ብሎ የምናገኘው Beat(ምት) Accent(አክሰንት) ተብሎ ይጠራል።

ለምሳሌ ያህል ከታች የተቀመጡት መዝሙሮች ላይ Accents(አክሰንቶቹ) የት እንዳሉ በአክሰንት ምልክት ( > ) ተገልጾአል።










ከአንደኛው አክሰንት እስከ ሌላኛው አክሰንት ድረስ ያለው Beat(ምት) ሙዚቃውን እኩል Measure(ርቀት) ላይ ይከፍለዋል። ይህም ርቀት Bar(ባር) ተብሎ ይጠራል። አንደኛው Bar(ባር) ከሌላኛው Bar(ባር) ለመለየት Bar-line (ቋሚ ወይም መከፈያ መስመር) እንጠቀማለን።





በባር መጀመሪያ ላይ የምናገኘው ምት Accent (አክሰንት) ተብሎ ሊጠራ ይችላል።




ነገር ግን ዜማው ሁል ጊዜ በአክሰንት (Accent) ላይጀምር ይችላል።ይህም ደግሞ off beat ወይም up beat ተብሎ ይጠራል።



Double bar(ድርብ ቋሚ መስመር) በአንድ ዜማ መጨረሻ ላይ የሚገኝ ድርብ ቋሚ መስመር ነው።




እንዲሁም ዜማው የሚደገም ሲሆን የሚደገመውን ዜማ የሚያሳይ ምልክት ከድርብ ቋሚ መስመሩ (Double bar) ፊት ለፊት ይቀመጣል።

ምልክቶቹም 𝄆 𝄇 ናቸው።



በተጨማሪም ሌሎች ምልክቶች አሉን። እነርሱም እንደ ሚከተሉት ናቸው።

1. D. C. = Da capo (ዳ ካፖ) ማለት ዜማውን ከመጀመሪያ ጀምረህ ድገም(ሚ)።
2. D. C. al Fine = Da capo al Fine (ዳ ካፖ አል ፊኔ)ማለት ዜማውን ከመጀመሪያ ጀምረህ “Fine” የሚል ምልክት እስከምታገኝበት(ኚበት) ድረስ ደግመህ ተጫወት(ቺ)።



3. Fine = (ፊኔ)ማለት መዝጊያው ወይም መጨረሻው ማለት ነው።
4. D. S. = Dal segno (ዳል ሴኞ) ማለት 𝄋 ከዚህ ምልክት ጀምረህ(ሽ)

እስከ መጨረሻው ድረስ ተጫወት(ቺ)።

5. D. S. = Dal segno al Fine (ዳል ሴኞ አል ፊኔ) ማለት 𝄋 ከዚህ ምልክት

ጀምረህ (ሽ) “Fine” እስከሚለው ድረስ ደግመህ ተጫወት(ቺ) ማለት ነው።


𝄎 ይህ ምልክት ከፊት የተጫወትከውን(ሽውን) ኮርድ ደግመህ(ሽ)

ተጫወት(ቺ) ማለት ነው።

♩=60 ይህ ምልክት የአንድ ሙዚቃ ፍጥነት በሜትሮኖም(metronom )

(የሙዚቃ ፍጥነት መለኪያ ) ሲለካ ምን ያህል መሆን እንደሚገባው ይገልፅልናል።

የእያንዳንዱ ዜማ የግዜ መለኪያ ( Time signature) በኖታው መጀመሪያ ላይ ተገልጾ እናገኘዋለን።



ከላይ በሥዕል እንደ ተገለጸው ሁለቱ የተለያዩ ወይም ተመሳሳይ ቁጥሮች አንዱ ከላይ አንዱ ከታች ተቀምጠዋል። የላይኛው ቁጥር የሚያመለክተው በአንድ ባር ውስጥ ስንት ምት እንዳለ ሲሆን የታችኛው ቁጥር ደግሞ የእያንዳንዱን ምት ዋጋ ወይም የጊዜ ርዝመት ያመለክታል።

$\frac{2}{4}$ የሚያመለክተው ሁለት Quarter-notes (ሩብ ኖት) ዋጋ ያላቸው ኖቶች በአንድ ባር ውስጥ ነው።

$\frac{3}{8}$ የሚያመለክተው ሦስት Eighth-notes (ስምንተኛ ኖት) ዋጋ ያላቸው ኖቶች በአንድ ባር ውስጥ ነው ።

## Doted note (ከኖት በኋላ የሚመጡ ነጥቦች)


የአንድ ኖት ዋጋ በሚከተሉት ሶስት መንገዶች ማስረዘም ይቻላል።

1. Tie note (በመስመር የተያያዙ ኖታዎች) ♩‿♪ = ♩ + ♪ ይህ ማለት

የመጀመሪያውን Quarter-notes (ሩብ ኖት) ከተጫወትክ በኋላ ድምጹን ሳይለወጥ ወይም ሳይለቀቅ Eighth-notes (የስምንተኛ ኖት) ዋጋ ወይም ርዝመት መጨመር ማለት ነው።




2. ከኖት ቀጥሎ አንድ ነጥብ በማስቀመጥ የኖታውን ግማሽ ዋጋ ወይም ርዝመት ድምጹ ሳይለወጥ ወይም ሳይለቀቅ መጨመር ማለት ነው።



ከነዚህ ከሁለቱ በአንደኛው መንገድ ሊጻፉ ይችላሉ ትርጉማቸው ወይም ዋጋቸው አንድ ዓይነት ነው።


3. ከኖት ቀጥሎ ሁለት ነጥብ በማስቀመጥ የኖታውን ግማሽ ቀጥሎ ሩብ ያህል ዋጋ ወይም ርዝመት ድምጹ ሳይለወጥ ወይም ሳይለቀቅ መጨመር ማለት ነው።




ከነዚህ ከሁለቱ በአንደኛው መንገድ ሊጻፉ ይችላሉ ትርጉማቸው ወይም ዋጋቸው አንድ ዓይነት ነው።

## PITCH (የድምጽ ከፍታ ወይም ዝቅታ)

የድምጽ ከፍታና ዝቅታን ለማሳየት Staff (ስታፍ) በሚባል በአምስት አግድም መስመሮችና በአራት ከፍት ቦታዎች ላይ ኖታዎችን በማስቀመጥ የድምጾችን ከፍታና ዝቅታ እንገልጻለን።




Line (መስመሮች)    Spases (ክፍት ቦታዎች)

ነገር ግን እነዚህ መስመሮችና ክፍት ቦታዎች የመስመሮቹንና የክፍት ቦታዎቹን ስም እንድንለይበት የሚረዳን ምልክት ካልተቀመጠ በራሳቸው የድምጽ ትርጉም አይሰጡም። እነዚህም ምልክቶች Clef or Key(ቁልፍ) ተብለው ይጠራሉ።

 Trable (G) Clef  Bass (F) Clef

ምንም እንኳን በርካታ ክሌፎች ቢኖሩም በአብዛኛው ጠቀሜታነት ያላቸው ከላይ ያየናቸው ሁለቱ ናቸው። በስታፍ ላይ ክሌፎቹ በሚቀመጡበት የመስመሩንና የክፍት ቦታዎችን ስም ይወስናሉ።



E G B D F    F A C E







G B D F A    A C E G

ኖታ ከነዚህ ከአምስቱ መስመሮችና ከአራቱ ክፍት ቦታዎች ውጪ ሊጻፍ ይችላል። ይህንንም ማድረግ የምንችለው Lager line (ተጨማሪ ትናንሽ መስመሮች) በመጠቀም ነው።

Middle C




Middle C




C(do) B(si) A(la) G(sol) F(fa) E(mi) D(re) C(do)

ከላይ እንደተመለከትነው የድምፆቹ ስም በእንግሊዝኛና በጣሊያንኛ ቋንቋዎች ሊጠሩ ይችላሉ። ይህም በዓለማችን ላይ የሚሰራበት ቋንቋ ነው።




በድምፅ ርቀት ላይ ከአንደኛው ድምፅ ወደ ሌላኛው ድምፅ ያለው በጣም ትንሹ ርቀት Semitone (ግማሽ ድምፅ) ይባላል:: ለምሳሌ ያህል ከላይ በተገለጸው የፒያኖ ሥዕል ላይ ከቁጥር 1-2 ወይም ከቁጥር 5-6,8-9 ያለው ርቀት Semitone (ግማሽ ድምፅ) ነው::

እንዲሁም ሁለት Semitone (ግማሽ ድምፆች) አንድ Full tone (ሙሉ ድምፅ) ይሰጣሉ:: ለምሳሌ ያህል ከቁጥር 1-3 ወይም ከቁጥር 5-7,9-11 ያለው ርቀት Full tone (ሙሉ ድምፅ) ነው::

## Scale (ስኬል)

ማንኛውም ዜማ የሚንቀሳቀስበት የራሱ የሆነ የተወሰነ በግማሽና በሙሉ ድምጾች ላይ የተመሠረተ የድምጽ ስብስብ ይኖረዋል:: ይህም Scale (ስኬል) ይባላል:: ይህም የድምፅ ስብስብ Scale (ስኬል) የራሱ የሆነ Home note (የመጀመሪያ) እንዲሁም የተወሰነ የድምፅ ርቀት Semitone (ግማሽ ድምፅ) እና Full tone (ሙሉ ድምፅ) ያካተተ ነው::



በዓለማችን ውስጥ በጣም ብዙ ዓይነት የተለያዩ ስኬሎች አሉ:: እንደ የአገሩና እንደ የባህሉ ልዩነት አላቸው:: ለምሳሌ ያህል የአውሮፓ የሩቅ ምስራቅ የአረቦች እንዲሁም የአገራችን ወዘተ የተለያዩ ዓይነት ስኬሎች አሉ::

ለምሳሌ ያህል 1. Diatonic scale

2. Pentatonic scale
3. Chromatic scale እና ሌሎችም ናቸው::

Diatonic scale በሰባት ድምፆች ላይ የተመሠረተ ሲሆን Pentatonic scale ደግሞ በአምስት ድምፆች ላይ የተመሠረተ ነው:: ምሳሌ

C Deatonic Major Scale
ሲ ዲያቶኒክ ሜጀር ስኬል




C Pentatonic Tezeta major scale
ሲ ፔንታቶኒክ ትዝታ ሜጀር ስኬል



አብዛኛው የሀገራችን ዜማዎች የተመሠረቱት Pentatonic scale ስኬል ላይ ነው። ምንም እንኳን እስካሁን በጥናት የተረጋገጡትና የሚታወቁት አራት ስኬሎች ብቻ ቢሆኑም ስኬሎቻችን ግን ቁጥራቸው ከዚህ ይበልጣል። በገፅ 107 ና 108 መመልከት ይቻላል።

1. ትዝታ 2. ባቲ 3. አምባሰል 4. አንቺ ሆየው ለኔ ወ.ዘ.ተ.

ከእነዚህም ውስጥ ትዝታ Major, Minor ሲኖረው

ባቲ ደግሞ Major, Minor ቅኝቶች ይኖሩታል።

<u>Pentatonic scales</u>

ትዝታ ሜጀር
Tezeta Major

ትዝታ ማይነር
Tezeta Minor

ባቲ ሜጀር
Bati Major

ባቲ ማይነር
Bati Minor






አምባሰል
Ambasel

አንቺ ሆየው ለኔ
Anchi Hoyew Lene




ከዚህ በታች ያሉት ሦስት ስኬሎች በመደበኛነት ከሚታወቁት ከትዝታ ባቲ ወ.ዘ.ተ. ስኬሎች ውጭ ሲሆኑ በገፅ 107 ና 108 ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው እነዚህ ስኬሎች ግልፅ የሆነ ስያሜ ስለሌላቸው ስኬሎቹን እንደሚከተለው አስፍረናቸዋል።



## Deatonic scale

ይህ ስኬል በሁለት ይከፈላል። እነርሱም

- Major (ሜጀር) እና Minor(ማይነር) ናቸው።
- Minor(ማይነር) ደግሞ ሦስት የተለያዩ ስኬሎች አሉት።
    1. Natural minor (ናቹራል ማይነር)
    2. Harmoic minor (ሃርሞኒክ ማይነር ) እና
    3. Melodic minor(ሜሎዲክ ማይነር) ናቸው።

Deatonic scales

ሜጀር
Major




ናቹራል ማይነር
Natural Minor




ሃርሞኒክ ማይነር
Harmonic Minor






ሜሎዲክ ማይነር
Melodic Minor




## Accidentals

አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆነ ድምፅን በግማሽ ወይንም በሙሉ ድምፅ ከፍ ወይም ዝቅ ለማድረግ ቢፈለግ ዜማው ከተመሠረተበት ስኬል


ውጭ የ# sharp (ሻርፕ) የ ♭ Flat (ፍላት) የ ♮ Natural (ናቹራል)

ምልክቶችን በመጠቀም ድምፅን መለወጥ ይቻላል።

# -sharp (ሻርፕ) ይህ ምልክት ድምፅን በግማሽ ከፍ ያደርጋል።


♭ - Flat (ፍላት) ይህ ምልክት ድምፅን በግማሽ ዝቅ ያደርጋል።


♮ -Natural (ናቹራል) ይህ ምልክት ድምፅን በግማሽ ከፍ ወይም ዝቅ ያደርጋል።


A Major
F# Minor
B ♭ Major
G Minor
E Major
C# Minor
E ♭ Major
C Minor
B Major
G# Minor
A ♭ Major
F Minor
F# Major
D# Minor
D ♭ Major
B ♭ Minor
C# Major
A# Minor
G ♭ Major
E ♭ Minor
F Major
D Minor
C ♭ Major
A ♭ Minor





# የፒያኖ ኮርዶች


Major
Minor
Dominant 7
Minor 7
C
C#
D
D#
E
F



Major 7
Minor 7-5
Diminished
Augumented
C
C#/Db
D
D#/Eb
E
F




Major
Minor
Dominant 7
Minor 7
F#
G
G#
A
A#
B


sus 4
7 sus 4
madd 9
mM7
C
C#/Db
D
D#/Eb
E
F




Major 7
Minor 7-5
Diminished
Augumented
F#/Gb
G
G#/Ab
A
A#/Bb
B

| ተ.ቁ. | የመዝሙር ርዕስ | የደራሲ ስም | የተደረሰበት ዓ.ም | ገፅ |
|---|---|---|---|---|
| 30 | አንተ ብቻ ነህ | ዝናሽና ኤልሳ | | 58 |
| 31 | አንተ ታላቅ ነህ | ታምራት ኃይሌ | | 52 |
| 32 | አንድ ነን በመንፈሱ | ፒተር ሹልትስ /ትርጉም/ | 1925 | 106 |
| 33 | አዬ ብቻኛው | ንጋቷ በቀለ | | 15 |
| 34 | አዲስ ሰው ሆንኩኝ | ሙሉ ወንጌል | | 93 |
| 35 | ኢየሩሳሌም | ደርጀ ከበደ | | 32 |
| 36 | እናምናለን በመስቀሉ | ዮሐንስ ተስፋዬ | 1966 | 26 |
| 37 | እንደ ማርያም ልሁን | የሻለቃ ግርማይ ቤተ | | 114 |
| 38 | እንደተቀበልኩት ምህረት | ተስፋዬ ጋቢሶ | | 102 |
| 39 | ካልባርከኝ | ፅዮን መዘምራን | | 80 |
| 40 | ክብር ለሆነን ጌታ | ተስፋዬ ጫላ | | 120 |
| 41 | ክብር ክብር | ታምራት ኃይሌ | | 54 |
| 42 | ክብር ይገባሃል | ጌታቸው አለማየሁ | | 50 |
| 43 | ወንጌላችን ገና | ጌታያውቃል ግርማይ | | 96 |
| 44 | ዘይትህን በመ፥ቅረዜ ሙላ | ትርጉም | | 18 |
| 45 | ዝናህ የገነነ | መሰረት ፅጌ | 1966 | 47 |
| 46 | ጌታ ለኛ ያረገው | ጌጃ ቃለ ህይወት | | 112 |
| 47 | ጌታ አምላካችን | | | 90 |
| 48 | ግሩም ነው ድንቅ ነው | | | 88 |
| 49 | የአምላክ ዋጋው | ሸዋዬ ዳምጤ | | 64 |
| 50 | የኃያልን ኃያል | ተስፋዬ ጫላ | | 60 |
| 51 | ያዲስ ኪዳን በግ | መሰርት ፅጌ | 1966 | 48 |
| 52 | ይመስገን ጌታ ይመስገን | የፅዮን መዘምራን | | 86 |
| 53 | ይብዛልህ እንጂ | ቤተልሔም ወልዴ | | 68 |
| 54 | ድሉ የጌታችን ነው | የመ/ክ/ዘማርያን | | 22 |
| 55 | ድንቅ ነው ለኔ ጌታ | ታምራት ኃይሌ | | 28 |



SONOS SHOP JERUSALEM